## ፍትሕ በዕብሪት ሲረገጥ በዝምታ ከታለፈ ሁሉም ዜጋ የአፈና ሰለባ ይሆናል።

*የሀገር እና የወገን አለኝታ በሆኑት የቅንጅት መሪዎች ላይ ወያኔ የሰጠውን እንበለ-ሕግ ብያኔ በመቃወም ከቅንጅት ካናዳ ድጋፍ ቻፕተር የተሰጠ መግለጫ*

ዓርብ አፕሪል 6 2007

በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ጥበቃ መርሆዎች እና በዓለም ዙሪያ ብዙ ሀገራት በሚገዙባቸው ሕግጋት መሠረት “ማንኛውም ሰው ወንጀለኛ መሆኑ በማያጠራጥር ሁኔታ በሕግ እስካልተረጋገጠ ድረስ ነፃ ነው” የሚለው ፅንሰ ሃሳብ ለወያኔ መሪዎች እና ለፍርድ ሥርዓቱ ከ17 ዓመታት በሁዋላ ዛሬም እንግዳ ነው። የወያኔ ካድሬ ዳኞች በቅንጅት መሪዎች ፣ በሰብአዊ ጥበቃ ተወካዮች እና ጋዜጠኞች ላይ በዚህ ሳምንት ሰጡ የተባለውን ብይን ጠ/ሚኒስተሩ ከነገረን ከርሟል። ሰውዬው “እነኝህን ሰዎች ፈረንጅም አበሻም አያስፈታቸውም” ብሎ የደነፋው ገና ያኔ መሪዎቻችን ማጎሪያ ቤት በተወረወሩበት ሳምንት ነበር ። ጨዋታው የአደባባዩን በጆሮ እንዲሉ መሆኑ ነው።

ከግንቦት 97 ምርጫ በፊትም ይሁን በሁዋላ የዚህ ወይም የዚያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት አባል ወይም ደጋፊ በሚል የወያኔ ፀጥታ ሠራተኞች አፍነው ወደ ማጎሪያ የወረወሩት ዜጋ በማግስቱ ታትመው በሚወጡ የወያኔ ዜና አውታሮች ፍረዱን መቀበሉ የተለመደ አሰራር ሆኖ ቆይቷል።
ጠ/ሚንስትሩ ፣ የፍትህ ሚንስትሩ ፣ አቃቤ ሕጉ ፣ ፖሊስ አዛዡ…ወዘተ ሁሉም የወያኔ ሹም እየተሽቀዳደመ በቁጥጥር ሥር ስለዋለው ዜጋ ወንጀለኛነት ይሰብካል። ሹማምንቱ ወዲያውኑ የማይነግሩን ነገር ቢኖር የቅጣቱን መጠን ብቻ ነው። የቅጣትን ዓይነት በሚመለከት መለስ ዜናዊ በቅርቡ ጣት እና እጅ ሳይቀር እቆርጣለሁ ያለው እንደሚገኝበት በዚህ አጋጣሚ ሊጠቀስ ይገባዋል። እርግጥ ነው የፖለቲካ ተቀናቃኞቻቸውን እና የተቀናቃኝ ደጋፊ ብለው የጠረጠሩትን ዜጋ ጣት እና እጅ መቁረጥ በአፍረቃ አዲስ ነገር አይደለም። በምእራብ አፍሪቃ የሴራሊዮን አማፂያን በደረሱበት መንደር ሁሉ የህፃናት እና የሴቶችን ጣት እና እጅ እየጎመዱ ዓለምን እጅግ የዘገነነ ድርጊት እንደፈፀሙ የምናውቀው ነው። በዩጋንዳም ቢሆን ሎርድ ሬሲስታንስ አርሚ የተሰኘው አማፂ ቡድን በተመሳሳይ እጅን እግር ሲቆርጥ ቆይቷል። የነኝህን ጣት ቆራጮች አድራጎት የመረመሩ የስነ ልቡና ጠበብት እንደተስማሙት በወገን ላይ ቀርቶ በማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ላይ ይህን አይነቱን ዘግናኝ ድርጊት የሚፈፅም ወይም መፈፀም የሚያስብ ሰው አይምሮው ትክክል መሆኑ አጠራጣሪ ነው። የወያኔው መሪ ጣት ቆረጣውን እንደ ተጨማሪ የማሸበሪያ ታክቲክ አድርጎ ቢጠቀምበት የሚገርም አይደለም ለማለት ያህል ነው። ብጤዎቹ ሲፈፅሙት የነበረ ጉዳይ ነውና።

በዚህ ረገድ የወያኔ ፍርድ ቤቶች ድርሻ ወንጀለኛ መሆኑ ቀድሞውኑ ፀድቆ የቀረበላቸውን ዜጋ ወንጀለኛነቱን በሰነድ ማፅናት ብሎም የቅጣት ብይን ሰጥቶ ጉዳዩን መቋጨት ይሆናል። በዚህ አይነቱ የጫካ ፍርድ ሥርዓት ብዙሀን ዜጎች ካላንዳች የፍርድ ቤት ትእዛዝ በፈለገ ጊዜ በቁጥጥር ሥር ይውላሉ ፣ ይገረፋሉ ብሎም ይገደላሉ። የት እንደደረሱ ደብዛቸው ጠፍቶ የቀረ እጅግ ብዙ ናቸው። ቅንጅት ከሕዝብ ጋር እየተቋደሰ ያለው ይህንን መሪር ፅዋ ነው። የቅንጅት መሪዎች የሰቆቃው ገፈት ቀማሽ የሆኑትም የሕዝብ ወገን ፣ የሕዝብ አለኝታ በመሆናቸው ነው።

ባለፈው አፕሪል 4 እና 5 2007 በቅንጅት መሪዎች እና በሌሎች ንፁሀን ዜጎች ላይ የተላለፈው ኢ-ፍትሐዊ ብይን ብዙ ዜጎች ከጠበቁት ውጭ የመጣ ድንገተኛ ውሳኔ አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ ከሚያውቀው ፣ ዘረኝነት እና በቀል ዋንኛ ባህሪው ከሆነ አፋኝ መንግሥት የተላለፈ ሌላ ዜና ከመሆን የሚያልፍም አይደለም። የሕዝብን ሕሊና ይበልጥ የሚያሳዝነው የወያኔ ዕብሪት ገደብ ማጣቱ እና በዚህ ዓይነት መረን የለቀቀ አፋና ስርዓት እየተገዛን የምንኖረው እስከመቼ ነው የሚለው ጉዳይ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

ፍርሀት እና መሸማቀቅ ከነገሰበት የአፈና ቀንበር ይታደጉኛል ፣ ሰላም እና ብልፅግና ያጎናፅፉኛል በሚል ፅኑ ተስፋ የመረጥካቸው ውድ መሪዎችህ እጅግ ፈታኝ ከሆነ ችግር ላይ መውደቃቸው ካንተ የተሠወረ አይደለም። ወያኔ በጠመንጃ እና በአፋኝ የስለላ መረቡ ተመክቶ በገሀድ አደባባይ ወጥተህ ፣ በወግ በማዕረግ መርቀህ የሾምካቸውን ብርቅ ልጆችህን ለማረድ ቢላዋ እየሳለ ነው። በዚህም ያንተ የሰላም ወዳዱ ሕዝብ ፈቃድ እና ፍላጎት እንዳይፀና ለማገድ ወያኔ በወጠነው የአሸባሪነት ጎዳና ቀጥሎበታል። ማልደህ አደባባይ በመውጣት ለመብትህ እንዲቆሙ ሳታመነታ በመረጥካቸው ልጆችህ ላይ የሚቃጣ ማናቸውም ጥቃት በአንተ ላይ እንደተፈፀመ ያህል መሆኑን ወያኔ ዘንግቶት ይሆንን? በዕብሪት የታወረው ወያኔ በንቀት እና በማን አለብኝነት የሚፈነጩውስ እስከመቼ ነው?

አምባገነን ገዢዎች ሽብርን እንደ አገዛዝ ስልት ለመጠቀም ሲመርጡ በአንድ በኩል ሕዝብ አመኔታ እንደነፈጋቸው ብሎም ከሕዝብ እጅግ ተነጥለው በራሳቸው የቅዠት ዓለም እንደሚባዝኑ ያመለክታል። በአሸባሪ አድራጎታቸው ተሸማቆ ሕዝብ ከነፃነት ትግሉ የሚያፈገፍግም ይመስላቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ለሕዝብ ሰብአዊ መብት መረጋገጥ በቁርጠኝነት የተሰለፉ የሕዝብ ወገኖችን ተስፋ የሚያስቆርጡ ይመስላቸዋል። የዲሞክራሲ ሽታ ደብዛው በጠፋባት አገራችን እየተፈፀመ ያለው ይኸው ነው። በዓለማችን በየዘመኑ ብቅ እያሉ የከሰሙ አምባገነኖች ታሪክ የሚያረጋግጠውም ይህንኑ ሃቅ ነው።

የሰብአዊ መብት ጠበቃ ኬን ሳሮ ዊዋ ከሌሎች ስምንት ባልንጀሮቻቸው ጋር በናይጄሪያው ፍፁማዊ አምባገነን ጄኔራል አባቻ የዕብሪት ውሳኔ በስቅላት መገደላቸውን ዓለም በመሪር ሐዘን ያስበዋል። በኔልሰን ማንዴላ እና በትግል ጓዶቻቸው ላይ በደቡብ አፍሪቃ የተፈፀመው ሰቆቃ ሕዝባዊ አመኔታ ባተረፉ ዜጎች ላይ ግፈኛ አምባገነኖች ለሚያደርሱት ዕብሪት የተመላበት አፈና ጥሩ ምሳሌ ነው። የቺሊ ሕዝብ ፍትሐዊነቱ በተረጋገጠ ዲሞክራሲያዊ ምረጫ ለስልጣን ያበቃቸው ሳልቫዶር አዩንዴ እና ደጋፊዎቻቸው የአምባገነኑ ጄኔራል ፒኖቼ አረመኔአዊ ጭፍጨፋ ሰለባ ሆነው እንደነበረም ዓለም ይመሰክራል። ይሁንና በሀገራችን የተፈራረቁት አምባገነኖችም ሆኑ የናይጄሪያው አባቻ ፣ የደቡብ አፍሪቃው ፒክ ቦታ ወይንም ጄነራል ፒኖቼ በግፍ ተግባራቸው የዜጎቻቸውን ሕሊና እያሳዘኑ ለዘላለም ሊቀጥሉበት አልቻሉም።

የወያኔ ጭካኔ በትር ለሰላም በቆሙ፣ ለፍትህ በተሟገቱ ንፁሀን ዜጎች ላይ ሲመተር ይህ የመጀመሪያው አይደለም የመጨረሻውም አይሆንም። ሕዝብ መሪዎቼ ናቸው ብሎ ለመረጣቸው ቅን ዜጎች አክብሮትን የነፈገ ወያኔ ከምንም ጥፋት የማይመለስ መሆኑ ግን ልብ ሊባል ይገባል። ይህ የወያኔ አድራጎት በጅምላ በመላው ዜጋ ላይ እንደተፈፀመ የሚቆጠር የንቀት እና የእብሪት እርምጃ ነው የምንለውም ለዚህ ነው። በእስር እየተንገላቱ ያሉት የቅንጅት መሪዎች የግል ኑሯቸውን አሸንፈው በኢትዮጵያ የኑሮ ደረጃ ለሌላ የሚተርፍ በቂ ጥሪት ያፈሩ ፣ የተደላደለ ሕይወት የነበራቸው ፣ በእውቀት እና ችሎታቸው ብቃት ዓለም ሳይቀር የመሰከረላቸው ባለሙያዎች ናቸው።

ውድ ወገናችን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ

የሩቅ እና የቅርብ ታሪካችን በውል እንደሚያረጋግጠው ሃይማኖት እና ዘር ወይም ጎሳ ሳይለየን በሰላም እና ተቻችሎ በአንድነት በመኖር ለዜግነት ክብራችን እና ለነፃነታችን ስንታገል ኖረናል። አኩሪ ታሪካችንን ለመጠበቅ ወደር በማይገኝለት ጀግንነት እና አትንኩኝ ባይነት የታገሉ ብሎም ትግሉን የመሩ የትውልድ ባለአደራዎች ሰብአዊ ክብርን ከሚያዋርድ ጠላት ፊት ተንበርክኮ ከመኖር ቆሞ መሞትን የመረጡ መንፈሰ ጠንካራ ዜጎች ናቸው።

የቅንጅት መሪዎች ለወያኔ የሸፍጥ አካሄድ ከምንንበረከክ ትግሉ የጠየቀውን መስዋዕት መክፈል ይቀለናል ብለው በፅናት የቆሙት ትናንት በምርጫ 97 የሰጠሀቸውን የታሪክ አደራ በክብር ጠብቆ ለማቆየት ነው። እውነትም አትንኩን ባይ መሆናችንን ፣ እውነትም ለነፃነታችን ቀናኢ መሆናችንን እውነትም ከግል ድሎት እና ምቾት ይልቅ የአገር እና የወገን ክብር ይበልጣል የሚል የማይበገር መንፈስ ያለን ነፃነት አፍቃሪ ሕዝቦች መሆናችንን መሪዎቻችን መልሰው አረጋግጠውተል።

እያንዳንዱ ዜጋ በዚህ ፈታኝ የነፃነት ትግል ማዕበል ውስጥ የቆመበት ስፍራ የማንነቱ ማረጋገጫ ይሆናል። ተንበርክኮ መኖር ወይም ቆሞ መሞት ምርጫው የያንዳንዱ ዜጋ ነው። ወደር በማይገኝለት መስዋዕትነት ተጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ በመሸጋገር ላይ ያለውን የነፃነት ክብር መልሰን ለማረጋገጥ እያንዳንዳችን በቁርጠኝነት ልንሰለፍ ይገባል። ነፃነት ወዳድ ነን ፣ አትንኩን ባይ ነን እያልን ለዚህ ክብር ያበቁንን የጥንት እና የዛሬ ጀግኖችን መዘከር ብቻ ለህልውናችን ዋስትና አይሆንም። የፖለቲካ ድርጅቶች ፣ የሙያ እና ሁሉም የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች  ኢትዮጵያን ለመታደግ በጋራ የሚቆሙበት እና ትግላቸውን ይበልጥ አስተባብረው የሚራመዱበት ሌላ ቀጠሮ የማይሰጥበት ጊዜ ዛሬ ነው።

በመጨረሻም ሁሉም ዜጋ በሕግ ፊት እኩል እንዲሆን ብሎም የሕግ የበላይነት በፅኑ ሕዝባዊ መሠረት ላይ እንዲቆም መታገላችሁ እንደወንጀል ተቆጥሮ በወያኔ ማጎሪያ ለተዘጋባችሁ መሪዎቻችን ፣ የሰብአዊ መብት ጠበቆች እና ጋዜጠኞች! ወገናችሁ በዘላቂ ሰላም እና ብልፅግና የእፎይታ ሕይወት እንዲገነባ ለማስቻል የቀየሳችሁት ራዕይ እውን እስከሚሆን ድረስ ሁላችንም ላንዲት ሰኮንድ እንኳ አርፈን እንደማንቀመጥ ትገነዘባላችሁ። የሕዝብን ከበሬታ እና ፍቅር መጎናፀፋችሁ ገሀድ ሃቅ በመሆኑ በያዛችሁት የመንፈስ ጥንካሬ ትግሉን መርታችሁ ለድል እንደምታበቁን ቅንጣት አንጠራጠርም።

## <u>ፍትህ እና ሰብአዊ ክብር የሚረጋገጡት በሕግ የበላይነት ብቻ ነው</u>